# ከኪዳናዊ ዮናስ አበበ፡ በፌስ-ቡክ መድረካችን ላይ የቀረቡ ጥያቄዎች፡-

በእውነት መልስ ስለሰጠኸኝ(ሺኝ) አመሰግናለሁ። መጻሕፍቱን እስካገኝ፡ የነዚህን ጥያቄዎች መልስ ብትሰጠኝ(ጪኝ) ካላስቸገርኩ? የምጠይቀው፡ መጻሕፍቱ ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ፤ ግን እማገኛቸው፡ ከወር በኋላ ስለኾነ ነው የቸኮልኩት፤ ከይቅርታ ጋር። ጥያቄዎቼ በተለያዩ ግዜ ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በድምፅና በምሥል፣ እንዲሁም በonline ላይ የተለቀቁ ጽሑፎች ላይ ካየሁትና ካነበብኩት የተነሣ ነው።

እነሱም፡-

፩. ቅድስት ድንግል ማርያምን፡ "እምናመልካት!" ሲባል፡ ምን ለማለት ነው?

፪. መጽሐፍ ቅዱስ፡ ብዙ የተሳሳተ እና ለኢትዮጵያውያን የማይመለከት ነገሮች እንዳሉበት ተገንዝቤአለሁ እና እንዴት እየለየሁ ማንበብ እችላለሁ?

፫. "የሰው ልጅ፡ ብቁ ከኾነ፡ እንደማይሞት.." የተባለው ነገር፡ ባልሳሳት፡ የሥጋዊን ሞት መሰለኝ፤ (እንደ ሄኖክ) እና "የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዜና ዕረፍት" የሚባለው ነገር እንዴት ይታያል?

፬. ሌላ ያልገባኝ፣ የነፍስ እና የመንፈስ ልዩነት ምንድነው?

፭. "እግዚአብሔር፡ በእውነት እና በመንፈስ ነው፡ መመለክ የሚፈልግ!" ከተባለ፡ አባታችን እና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአካል ይመጣል? አይመጣም? (ይቅርታ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ አዲስ ማየት ስለ ጀመርኩ ነው።)

፮. "ገነት፡ የነፍስ መኖሪያ፣ መንግሥተ ሰማያት ደግሞ፡ ከትንሣኤ በኋላ!" የሚባለው፡ ምን ያህል እውነት ነው? ወይም፡ "'ሲኦል' የሚባል የለም! እየሩስአሌም ላይ ያለ (የነበረ) ነው!" ስለሚባለው እና "እግዚአብሔር ጨክኖ፡ ፍጡሩን በዘላለማዊ እሳት አይተውም!" ስለሚባለው ነገር፡ ምን ማለት ይቻላል?

፯. ምሥራቃውያን፡ የመንፈስ የኾኑን ነገሮች የማውጣት ተሰጥኦ እንዳላቸው ተረድቻለሁ። ታድያ! "የነሱ ተመሥጦ እና ዮጋን የመሳሰሉ ነገሮች፡ የሰይጣን መሣሪያዎች ናቸው!" የሚሉ አሉ። ከኾነ፡ ሌላ ትክክለኛ ተመሥጦ አለ?

በመጨረሻም፡ ዛሬ ይህን ጥያቄ ከመጠየቄ በፊት፡ በቁጥር ፩/፳፻፭ ዓ.ም በወጣው ቃለ ዐዋዲ መለኮታዊ ምዕዳን መሠረት፡ ዛሬ ነሓሴ ፱ ቀን፥ ፳፻፰ ዓ.ም፡ **የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ኾኛለሁ (ነኝ)።** አኹን፡ ኹሉን ነገር፡ መድኃኔ-ዓለም እንደሚገልጥልኝ እና እንደሚረዳኝ አምናለሁ። አኹን፡ ምን ማድረግ አለብኝ? ማለት፡ ኹሉን ነገር፡ በራሴ፡ ውስጤ የሚነግረኝን ላድርግ? ወይም፡ መመሪያ ነገር ካለ፣ ያለ አይመስለኝም፣ ግን፡ የኾነ ነገር በለኝ (በይኝ)። በተረፈ፡ መልሱን ስትልክልኝ(ኪልኝ)፡ አንቱታው ቢቀርልኝ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ።

ጤና ይስጥልኝ፣ ጋሽዬ! እንኳን አደረሰን!

እንደሚታወቀው፡ ቀደም ሲል፡ ጥያቄዎችን አቅርቤ ነበር። አኹን ደግሞ፡ ይህንን ጻፍኹ፡-

ሀ. በመጀመሪያ ይቅርታ፣ ጋሼዬ! በዚያን ግዜ፡ "አንተ/አንቺ" የሚሉ ቃላት የተጠቀምኩት፡ ጥያቄው ማን ጋር እንደሚደርስ፡ በእርግጠኝነት ስላላወቅኹ ነው። (በተወሰነ መልኩ፡ ለአንተ እንደሚደርስ ብገምትም)፡ ምንም እንኳን፡ ለጥያቄ መልስ የሚሰጥ፡ እግዚአብሔር ቢኾንም።

በ. አኹንም ይቅርታ የምጠይቀው " መመሪያ ነገር ካለ፣ ያለ አይመስለኝም " የሚል ቃል የተጠቀምኹት፡ "በውስጣችን የተጻፈ ሕግ እና ሥርዓት አለ!" ከሚል አንጻር ነው እንጂ፡ ማቃለሌ አይደለም፤ ጋሼዬ! እግዚአብሔር የመረጠዉን፡ እኔ እንዴት ላቀል ይቻለኛል? ችኾላዬም በመለስክልኝ ተደስቼ ስለነበር ነው። ይህንን የይቅርታ ጽሑፍ የጻፍኹትም፡ ለመግባባት እንጂ የጻፍኩት፡ "'ስሕተት ነው!' ብየ፣ ተጸጽቼ አይደለም፤" ስል በትሕትና ለመግለጽ እወዳለሁ።

ገ. መጻሕፍት ጠይቄ ነበር፤ በቅርቡ የሚደርሱኝ ይኾናሉ። እንደመታደል፡ በኀዋው አውታር የሚተላለፈውን ጽሑፍ፡ በሙሉ ለማግኘት በቃሁ። ምን ያህል ደከምክ እና እግዚአብሔር አባታችንና እናታችን ምን ያህል እንደሚወዱን እንድናውቅ የሚያስችሉና እኛ ደግሞ ምን ያህል እንደራቅን የሚሳዩ ናቸው። ጽሑፎቹን ሳነብ፡ መጻሕፍቶቻችንን ለማንበብ ጉጉቴ እየጨመረ መጣ። በዚህ አጋጣሚ፡ ስለአገልግሎትህ፡ "እግዚአብሔር ይስጥልኝ!" ለማለት እፈልጋለሁ አገልጋዬ።

ደ. የጥያቄዎቹ መልስም፡ ከጽሑፎቹ፡ ከበቂ በላይ ተጽፎ አግኝቼአለሁ። ለዚህም፡ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። ሌሎች ሰዎችም፥ ወይም፡ ተቋማት፡ የሚልኩትን ጥያቄና ትችት፥ ወይም ሀሳብ ለመመለስ፡ በተለያዩ ምክንያቶች ዘግይተው እንደሚመለሱም ተመልክቼአለሁ። ስለዚህ፡ "አንድ ቀን ይመለሱልኛል!" ብየ ያሰብኩትን፡ እነሆ፡ መጻሕፍቱ፥ ወይ ጽሑፎቹ ውስጥ ካሉ፡ ይህንን በመመለስ አትድከም፣ ጋሼዬ!

፩. እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያ ተዋሕዶ አማኞች፡ ንስሓችን፡ ቅጽበታዊ ነው? ወይስ፡ የግዜ ርዝመት አለው? ማለት ስዓታት ወይ ቀናት?

፪. እኛ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያ ተዋሕዶ አማኞች፡ የአክብሮት ቃላትን (አንቱታን የመሳሰሉ)፡ ላላመኑ ሰዎች እንደምንጠቀም ይታወቃል። ታድያ! እኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን ያመነው፣ አምነንም የምንኖርበት፡ እንደአርቶዶክሳውያን የትሕትና ቃላትን መጠቀም አለብን? (ለምሳሌ፡ "እኔ እማልረባ ነኝ! ወይ ከንቱነኝ!")

፫. በመጨረሻም፡ እንደማሳሰብያ፡- ጋሼዬ! መጻሕፍቶቻችን እኮ፡ በአገሪቱ እንደልብ አይገኙም፤ ይህ የኾነዉ ስለምንነው?

፬. ሌላው፡ እኔ በምማርበት፡ ባሕር-ዳር መካነ-እእምሮ፡ የግእዝ ትምህርት፡ በሳምንት፡ አንድ ቀን እንደሚሰጥ ይታወቃል። ታድያ! ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በዚህ ላይ ያላት ዕቅድ ምንድን ነው?

ለዛሬ ጨረስኹ። መጻሕፍቱን አንብቤ እንደጨረስኹ፡ ዳግመኛ የምጽፈው ይኖረኛል። (ስለ ፊደል አጠቃቀም ሥርዓት ይቅርታ)። እወድህአለሁ። ደኅና ኹን! እግዚአብሔር ይስጥልኝ። ኪዳናዊ ዮናስ አበበ

## ለእነዚህ፡ ለኪዳናዊ ዮናስ አበበ ጥያቄዎች፡
## ከኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት የተሰጠ መልስ፡-

ይድረስ፡- ለኪዳናዊ ዮናስ አበበ!

በእግዚአብሔር ስም፡ ኢትዮጵያዊ ሰላምታችንን እናቀርብልሃለን።

በፌስ-ቡክ መድረካችን ላይ ለላክህልን መልእክትና ላቀረብህልን ጥያቄዎችህ እግዜር ይስጥልን።

ይህ የመልስ እ-ጦማር፡ በጊዜው ተዘጋጅቶ ሣለ፡ ሳይተላለፍልህ የዘገየው፡ በቅርቡ፡ በአገር ውስጥ በታወጀው፡ ያስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ምክንያት፡ የኀዋ አውታር መገናኛችን ተቋርጦ ስለነበረ መኾኑን፡ ከይቅርታ ጋር እንድታውቀው ይኹን!

የጥያቄዎችህ መልሶች እንደሚከተለው ሠፍረዋልና ተመልከታቸው፡-

፩. ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ፍጹም አምላክም፥ ፍጹም ሰውም የኾነውን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ መጀመሪያ፡ ከፍጥረተ-ዓለም አስቀድሞ፡ እግዝእተብሔር እም ኾና፡ በመለኮትነቱ፥ በመጨረሻም፡ ከፍጥረተ-ዓለም በኋላ፡ ድንግል ማርያምን ተዋሕዳ፡ በሰውነቱ፡ ከእግዚአብሔር አብ ስለወለደችው፡ በዚህ መለኮትነቷ እና ትስብእትነቷ፡ የአንዱ እግዚአብሔር፡ ተባዕታዊ አካልና ባሕርይ እንደኾነው፡ እንደ"እግዚአብሔር አብ"፤ እርሷም፡ የአንዱ እግዚአብሔር፡ እንስታዊ አካልና ባሕርይ የኾነች፡ "እግዚአብሔር እም" ስለኾነች፤ እንዲሁም፡ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ እና ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ስለኾነች፡ "እግዝእተብሔር መላኪት ናት!" ብለን እናመልካታለን።

የዚህን እውነታ፡ ዝርዝር ሓተታ፡ በተለይ፡ ከ፲፮ቱ (ከዐሥራ-ስድስቱ) መለኮታውያት የዐዋጅ ቃሎች ጽሑፎቻችን፥ አያሌዎች መልእክቶቻችንና በርካታ መጽሓፎቻችን ታገኘቸዋለህና፡ እነዚያን ተመልከታቸው።

፪. "ብዙ የተሳሳቱ እና ኢትዮጵያውያንን የማይመለከቱ ነገሮች እንዳሉበት ተገንዝቤአለሁ!" ያልከውን መጽሐፍ ቅዱስን፡ እንዴት እየለየህ ማንበብ የምትችልበትን፡ እውነተኛ መንገድ እንድናመለክትህ ከፈቀድህልን፡ መንገዱ ይኸውልህ!

ከላይ በ፩ኛው ተራ ቍጥር፤ በመጨረሻው አንቀጽ ውስጥ የተጠቀሱትን፡ የኢትዮጵያን የእምነትና የምግባር፥ የሥርዓትና የህልውና መዛግብት የኾኑትን ጽሑፎች፥ ባጭሩም፡ **ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** መሠረታውያት መመሪያ ሰነዶች የኾኑትን፡-

"የሃይማኖት" እና "የቃል ኪዳን"፥ "የእግዚአብሔር ምስጋና" እና "የድንግል ማርያም ሰላምታ" የተባሉትን አራቱን ጸሎታት አንብበህ፡ ስለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ምንነትና ማንነት፡ በሚበቃ በመረዳት ብቻ ነው።

፫. ከእኛ፡ የአንዳችን ብጤ [ዕሩቅ ብእሲ] የኾነው፣ አንተ፡ በስሙ የጠቀስኸው ሄኖክ፡ ራሱን፡ ለእግዚአብሔራዊው ሕይወት ለማብቃት በመቻሉ፡ ነፍሳዊውና መንፈሳዊው ብቻ ሳይኾን፡ ሥጋዊው ሞት ጭምር የማያገኘው መኾኑን፡ አንተም እንዳመንህበት እሙን ነው። እንዲያ ከኾነ፡ ታዲያ! ምንነቷና ማንነቷ፡ ከላይ በ፩ኛው ተራ ቍጥር የተገለጸው፡ "'የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዜና ዕረፍት' የሚባለዉ ነገር እንዴት ይታያል?" የሚል፡ ይህን የመሰለ ጥያቄን፡ አንተ እንድታነሣ፡ ለምን አስፈለገህ? እንዴትስ፡ ጥያቄውን ልታቀርብ ደፈርህ? ወይስ፡ ስለእርሷ እውነተኛ ማንነት፡ በዚያን ጊዜ፡ አንተም፡ ገና አላመንህም ነበርን?

እግዚአብሔር ይሞታል እንዴ? ራሱ፡ ሕያውና የሕይወት ምንጭ ስለኾነ፡ እንዴት ይሞታል? አይሞትም። ስለዚህ፡ እርሷም፡ በዚህ እግዝእተብሔርነቷና የእግዚአብሔር አካልነቷ አትሞትም። በእርሷ ዘንድ፡ ሞትና የሞት ዜና ዕረፍት የለባትም።

ፈጣሪ ልጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከእርሷ ሰው ኾኖ የተወለደበት ዋና ዓላማ፡ በመልኩና "ከእኛ እንደአንዳችን ኾነ!" ብሎ፡ ከሕይወትና ለሕይወት፥ በሕይወትም የፈጠረው ሰው፡ ራሱን፡ ላልተፈጠረለት ሞት፡ በፍላጎቱና በምርጫው ስለዳረገ፡ የዚህኑ ምውት ፍጡሩን፡ የሞት ፍዳ፡ በቤዛነት በመቀበል፡ ወደቀደመ ሕይወቱ ሊመልሰው ስለኾነ፡ እርሱ ልጇ ወዳጇ፡ ለዚሁ ሰው፡ በቤዛነት ሊሞትለት፣

እርሷ፡ እግዚአብሔር እም ግን፡ ለኢመዋቲነት እንደበቃው፡ እንደሄኖክ ኹሉ፡ እርሷም፡ ለእግዚአብሔር እናትነት የበቃችውን፡ ድንግል ማርያምን ተዋሕዳ ሰው ኾና የተወለደችበት ዋና ዓላማ፡ በመስቀል ላይ እንደፋሲካ በግ ታርዶና ደሙን አፍስሶ፥ በቤዛነትም ሞቶ፡ የእርሱና የፍጡሩ ሰው ጠላት ኾኖ፡ በመንፈስም፥ በነፍስም፥ በሥጋም፡ ለዝንተ-ዓለም ጦርነት ያወጀበትን፡ የክፋትና የጥላቻ ኃይል፡ ለአንዴና ለዘለዓለም፡ በፍቅርና በደግነት ትሕትና ድል ነሥቶ፡ የዘለዓለም ሰላምን የመሠረተ ልጇን ወዳጇን፡ እግዚአብብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን ልትወልድ ነው።

፬. አንዱ እግዚአብሔር፡ በመልኩ፥ እንዲሁም፡ "ከእኛ፡ እንደአንዳችን ኾነ!" ብሎ፡ ራሱን፡ "እግዚአብሔር አብ" እና "እግዚአብሔር እም" ብሎ በወንድነት እና በሴትነት እንደከፈለው ኹሉ፡ "አዳም" እና "ሔዋን" ብሎ፡ በወንድነት እና በሴትነት የፈጠረው አንዱ ሰው፡ እንደቅድስት ሥላሴ፡ በማሕፀን የተዋሓዱ፡ ሦስት አካላትና ሦስት ባሕርያት አሉት።

እነዚህም፡ በእየራሳቸው፡ ከእግዚአብሔር አብወእም የተገኘችው፣ ነባቢት፥ ለባዊትና ሕያውት የኾነችው፡ የነፍስ አካልና ባሕርይ ናት፤ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ከፀሓይ፥ ከነፋስ፥ ከውኃና ከመሬት የተገኘው የሥጋ አካልና ባሕርይ ነው፤ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የተገኘው፡ እውነት፥ ዕውቀትና ሕይወት የኾነው የመንፈስ አካልና ባሕርይ ነው።

እነዚህ፡ ሦስት አካላትና ባሕርያት፡ በእየራሳቸው ፈቃድና ምርጫ፥ ውሳኔና ድርጊት፡ እየራሳቸውን የቻሉ ቢኾኑም እንኳ፡ ሳይለያዩ፡ በተዋሕዶ፡ ፍጹም አንድ ኾነውና ተስማምተው ሊኖሩና ሊሠሩ የሚገባቸው ናቸው። ከተለያዩ፡ የየግላቸውና የጋራቸው ህልውና ይቀራል።

፫. እግዚአብሔርን በእውነት እና በመንፈስ ለማምለክ፡ እየራሳችንን ባበቃን ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ዘንድ ኹሉ፡ "የአባታችን እና የሰላማችን የኢየሱስ መሲሕ፡ በአካል ይመጣል? አይመጣም?" የሚለው ጥያቄ፡ በመጀመሪያ ነገር፡ በውስጣችን አይነሣም፤ አይቀርብምም። ምክንያቱም፡ እርሱ፡ አባታችን እና ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ በመንፈስ ቅዱስ መውረድ ምክንያት፡ ለአንዴና ለዘለዓለም መጥቶልናልና።

መንፈስ ቅዱስ፡ እንዲህ፡ ለቅጽበትም ሳይለየን፡ ምንጊዜም ዐብሮን አለ። ዐብሮን ሊኾን የቻለውም፡ **"ወዛቲ ይእቲ ቀዳሚት ሕይወት፤ ብፁዕ ወቅዱስ ውእቱ፡ ዘረከበ ክፍለ፡ በይእቲ ዕለት፡ እንተ ትቀድም መጺአ! እስመ አልቦ እንከ፡ ዳግመ፡ ሥልጣነ-ሞት ላዕለ እሉ።**

"ይህ [በመንፈስ የሚኾነው]፡ የፊተኛው ትንሣኤ ነው፤ በዚህ [በመንፈስ በሚኾነው]፡ በፊተኛው ትንሣኤ፡ ዕድል ፈንታ ያለው፡ ብፁዕና ቅዱስ ነው፤ ኹለተኛው ሞት፡ እንግዴህ ወዲህ፡ በእርሱ ላይ ሥልጣን የለውምና።" በሚለው ቃል መሠረት ነው። (ራእ. ፳፥ ፭-፯።)

ነፍሳችን፡ በሥጋዊው አካሏና ባሕርይዋ ባላት የዕውቀት ኃይል ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ በመንፈሳዊው አካሏና ባሕርይዋ የዕውቀት ኃይሏም የመጠቀም ፍላጎት ሲኖራት፥ ምርጫዋንም በዚያ መንገድ ስታደርግ፡ ይህን የመሰለው፡ የመንፈስ ቅዱስ እውነታ ኹሉ፡ በግልጽ ገሃድ ይኾንላታል፤ሕይወቱንም ልትኖረው ይቻላታል።

"የአባታችን እና የሰላማችን የኢየሱስ መሲሕ፡ በአካል ይመጣል? አይመጣም?" የሚለው ጥያቄ የሚያስቸግራቸው፥ የሚያውካቸውም፡ ነፍሳቸው፡ በሥጋዊው የዕውቀት ኃይሏ ብቻ የምትጠቀመው ናት። ነፍስ፡ በመንፈሳዊው አእምሮዋ ካልኾነ በቀር፡ ይህን፡ የኢየሱስ መሲሕን፡ በአካል የመምጣቱን ነገር፡ በሥጋዊው አእምሮዋ ልታስተውለውና ልትቀበለው፥ ልትመለከተውም አይቻላትም።

ይህን፡ የኢየሱስ መሲሕን፡ በአካል የመምጣቱን ነገር፡ በገሃድና በግዘፍ ማየቱን የሚፈልጉትና የሚጠብቁት፡ የሚያስፈልጋቸውም፥ ዕድሜውንና ዕድሉን ለማግኘት ከቻሉ፡ "ሙታን" የተባሉት፡ ሥጋውያኑና ዓለማውያን የኾኑት፡ የማያምኑት ናቸው። ማየቱም የሚያስፈጋቸው፡ እንደነዚህ ያሉት ናቸው፤ የዳግመኛ መምጣቱ ዓቢይ ዓላማ፡ አይተው፡ እንዲያምኑና ከመንፈስ ምውትነታቸው እንዲነሡ ለማድረግ ነውና።

እነዚያ፡ በመጀመሪያው የመንፈስ ትንሣኤ ሕይወት ውስጥ የሚገኙት አማኞቹ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ግን፡ በመምጣቱ ጊዜ፡ ሕያዋን በመኾናቸው፡ መነሣት ሳያስፈልጋቸው፡ በሕይወት እንዳሉ፡ በተመሠጡበት ብቅዓታቸው፡ ወደሰማይ በአየር ተነጥቀው፡ ከእርሱ፡ "ከአባታችን እና ከሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ" ጋር ዐብረው ይኾናሉ። (፩ተሰ. ፬፥ ፲፫-፲፰።)

፮. መቸም፡ ለእውነትም፥ ለሓሰትም፣ ለደግነትም፥ ለክፋትም፣ ለሕይወትም፥ ለሞትም፡ ተገቢው ዋጋ ተከፍሎና በኹለቱ ተፃራሪ ኃይላት መካከል የሚካኼደው ጦርነት፡ ከኹለት በአንደኛው ድል አድራጊነት አብቅቶ፡ የመጨረሻው ፍርድ የሚሰጥበት ቀን መምጣት ያለበት፡ አግባብ መኾኑ፡ ለማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር፡ ለአማኒውም፥ ለኢአማኒውም፡ አጠያያቂ አይደለም።

ሓሰትንና ክፋውን፣ ሞትንም የመረጡ ሰዎች ኹሉ፡ የእግዚአብሔር ትዕግሥቱ፡ እጅግ የበዛ ነውና፡ በንስሓ፡ ወደእውነት፥ ወደደግነትና ወደሕይወት ተመልሰው እንዲድኑ፡ ያ፡ የመጨረሻው የፍርድ ቀን እስኪመጣ፥ መጥቶም፡ ሰዎች ኹሉ፡ እንደየምርጫቸው ተለያይተው፡ የእግዚአብሔር የኾኑት፡ ለዘለዓለም ክብርና ሕይወት፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት፣ የሰይጣን የኾኑት ደግሞ፡ ለዘለዓለም ውርደትና ሥቃይ፡ ወደሰይጣን ገሃነም፡ ዓለም ሳይፈጠር ወደየተዘጋጀላቸውና ወደየተመደበላቸው ዓለም እስኪኼዱ ድረስ፡ በልዩ ልዩ ምክንያት፡ በእየጊዜያቱ፡ ከየሥጋ አካላቸው የሚለዩት ነፍሳት ኹሉ፡ ታዲያ! በየት ይቆዩ?

በግድ መቆያ ያስፈልጋቸዋል። ያ መቆያም፡ ለእውነተኞች፥ ለደጎችና ለሕያዋን፡ "ገነት" የተባለችው፡ ብሔረ ጻድቃን፥ ብፁዓንና ሕያዋን ስትኾን፥ ለሓሰተኞች፥ ክፋዎችና ሙታን ደግሞ፡ "ሲኦል" የተባለው መቃብረ ሓሳውያን [ኃጣኣን]፥ እኩያንና ሙታን ኾኖ፡ የአመክሮና የንስሓ ቦታ ነው።

"'ቤዝዎት እና ኵነኔ፥ ገነት እና ሲኦል፥ መንግሥተ-ሰማያት እና ገሃነመ-እሳት' የሚባለው የህልውናና የርእዮት፥ የአስተሳሰብና የአስተያየት የንጽጽር ዓለም የለም!" የሚያሰኘው ዘይቤ እኮ፡ ትክክል አይደለም ላይባል ይቻል ይኾናል። ምክንያቱም፡ ያ ሰው፡ በነፍሱና በሥጋው፥ በመንፈሱም፡ ፍጹም ዕውቀትና ፍላጎት፡ የሚያደርገው፡ የአስተሳሰብና የአስተያየት፣ የርእዮትና የህልውና ምርጫ፡ ለእርሱ፡ "እጅግ መልካም፥ የሚበጀውና የተስማማው ኾኖ ያገኘው፥ አምኖም የተቀበለው ሊኾን ስለሚችል ነው። ከዚህ እውነታ የተነሣ፡ የዚያ ሰው ህልውና፡ በእርሱ ርእዮት፥ አስተሳሰብና አስተያየት፡ ለእርሱ፡ ሓሰቱ፡ እውነት፥ ክፋቱ፡ ደግነት፥ ሞቱ፡ ሕይወት ኾኖ ስለሚያገኘውና ስለኾነለት፡ ከላይ የተጠቀሰው ዘይቤ ትክክል ነው ተብሎ፡ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል።

ስለዚህ፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ "ጸደቀ!" ወይም፡ "ተፈረደለት!"´ በዚህ አንጻር ደግሞ፡ "ተኰነነ!" ወይም፡ "ተፈረደበት!" ሲባል፡ ያን ውሳኔ፥ ወይም፡ ብያኔ፡ እግዚአብሔር እንዳደረገው ሳይኾን፡ ራሱ፡ ሰውዬው፡ በራሱ ላይ፥ ለራሱ፥ ከራሱ ያደረገው መኾኑ፡ በእርግጥ ሊታወቅ ይገባል።

በእግዚአብሔርማ በኩል፡ ፈቃዱና ፍላጎቱ፥ ዝግጅቱም ኹሉ፡ ፍጡሩ ኹሉ፡ አንድም ሳይቀር፡ ኹሉም እንዲድን ብቻ አይደለምን? አዎን! ነው እንጂ። እውነታው፡ ይህ ከኾነ ታዲያ! "መጥፋት"፥ ወይም፡ "ሞት" የሚባለውን ነገር ያመጣው፡ ራሱ ሰው በመኾኑ፥ ያም ደርሶ የሚፈጸምበት፡ በእየራሱ በኩል በሚያደርገው ምርጫና

በሚሰጠው ውሳኔ በመኾኑ፡ እውነታውን፡ ይኸው መንሥኤውና ኺደቱ፥ ውጤቱም እያረጋገጠ አይደለምን? አዎን! ነው እንጂ።

፯. ተመሥጦ፡ እንዳደረጉት ነው። በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ የሚካኼድ ተመሥጦ አለ፤ ይህ፡ ቅዱሱ ነው። እኛ፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** የኢትዮጵያ ልጆች የኾንን ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፡ የተቀበልነውና የምናምንበት፥ የምንከተለውና የምንፈጽመው፡ ይህንኛውን፡ የተቀደሰውን ዓይነት ነው።

በሰይጣናዊው ሓሰትና በርኩስ መንፈስ አምልኮ የሚካኼድ፡ የዚህ ተቃራኒ የኾነ ተመሥጦ ሊኖር ይችላል፤ እንዳለም ይታመናል፤ ይህ፡ ርኩሱ ዓይነት ስለኾነ፡ እኛ፡ እንቃወመዋለን እንጂ፡ አንቀበለውም።

ከዚህ በቀር፡ ከአምልኮ ጋር ሳይያያዝ፡ ለሥጋዊ ጤንነትና ጥንካሬ ብቻ ተብሎም፡ የሚካኼድ አለ። ይህን ዓይነቱን አንቃወመውም።

ተመሥጦ፡ እንደሌላው ምግባርና ሥርዓተ-ሕይወት ኹሉ፡ በሃይማኖት ላይ ካልተመሠረተ በቀር፡ እውነተኛ ተመሥጦነቱ ይቀራል። "የምሥራቃውያን" በለው፡ "የምዕራባውያን"፥ "የሰሜናውያን" በለው፡ "የደቡባውያን"፥ "የሴማውያን" በለው፡ "የካማውያን"፥ "የያፌታውያን" በለው፡ በመጨረሻ፡ ኹሉን የሚያጠቃልለው፡ "የኢትዮጵያውያን" ጭምር፡ ኹሉም፡ ከንቱ ይኾናል፡ አዎን! በእውነተኛ ሃይማኖት ላይ ካልተመሠረተ በቀር።

ለመኾኑ፡ "ተመሥጦ" ምንድር ነው? ጤናማው "ተመሥጦ"ማ፡ ነፍስና ሥጋ፥ መንፈስም፡ ፍጹም አንድ ኾነው፡ በአሳብ፥ በንግግርና በሥራ አንድ ኾነው ለመገኘት፥ ከአንድ የስምምነት ዓላማም ለመድረስ፡ ይስማሙ ዘንድ፡ በአንድ አግጣጫ ለማሰብ፥ ለመናገርና ለመሥራት፡ የጋራ ክርክርና የአስተያየት ልውውጥ፥ ውይይትና ምክክር የሚያደርጉበት ገበታ ነው።

ከዚያ፡ ለፍጹም ሕይወት ወደሚያበቃው "ተመሥጦ" ይደርሳሉ። እርሱም፡ በአንድ ሰው ሰውነት ውስጥ ያሉት፡ ሦስቱም አካላትና ባሕርያት፡ እነርሱም፡ ሥጋና ነፍስ፥ መንፈስ፡ በፍጹም እውነትና ዕውቀት፥ ፍቅርና ሰላም ተስማምተው፡ በተዋሕዶ ምስጢር፡ አንድ የኾኑበትን ሕይወት ለመኖር ያላቸውን ፍላጎታቸውንና ፈቃደኛነታቸውን፡ በምርጫቸውና በውሳኔያቸው አንድ መኾናቸውን፥ በተግባርም ሊፈጽሙት መቻላቸውን የሚያረጋግጡበት እውነታ ነው።

ከዚህ የመጨረሻ ግብ ለመድረስ ግን፡ በተመሥጦው ጊዜ፡ የሚካኼደውና የሚኾነው፡ ይህ ነው፡- መጀመሪያ "ነፍስ"፡ በራሷ አካላዊና ባሕርያዊ ፍላጎትና ፈቃድ፥ ምርጫና ውሳኔ፡ የሥጋዋን አካላዊና ባሕርያዊ ፍላጎትና ፈቃድ፥ ምርጫና ውሳኔ፡ ለመንፈሷ አካላዊና ባሕርያዊ ፍላጎትና ፈቃድ፥ ምርጫና ውሳኔ፡ ተገዥ ማድረጓን በቍርጥ ማረጋገጥ ይኖርባታል። ይህ እውነታ፡ እውን መኾኑ ሲረጋገጥ፡ "ተመሥጦው፡ እውነተኛ ኾኖ፡ ለፍጹሙ ሕይወት ዐበቃ!" ይባላል። በቃም።

"በመጨረሻም፡ ዛሬ፡ ይህን ጥያቄ ከመጠየቁ በፊት፡ በቁጥር ፩/፳፻፫ ዓ.ም በወጣው ቃለ ዐዋዲ መለኮታዊ ምዕዳን መሠረት፡ ዛሬ፡ ነሓሴ ፱ ቀን፥ ፳፻፰ ዓ.ም፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ኾኛለሁ (ነኝ)።" የሚለውን የምሥራች ቃል ሳነብብ፡ የተሰማኝ ደስታ፡ ታላቅ ነው።

"እብለክሙ፡- 'ከመ ከማሁ ይከውን ፍሥሓ በሰማያት፡ በቅድመ መላእክተ እግዚአብሔር፡ በእንተ አሓዱ ኃጥእ ዘይኔስሕ፡ ፈድፋደ፡ እምነ ተስዓ ወተስዐቱ ጻድቃን፡ እለ ኢይፈቅዱ ይነስሑ።

"እላችኋለሁ፡- እንዲሁ፡ ንስሓ ከማያስፈልጋቸው፡ ከዘጠና ዘጠኝ እውነተኞች ሰዎች ይልቅ፡ በንስሓ በተመለሰ፡ በአንድ ኃጢአተኛ ሰው፡ በሰማያት፡ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት፡ ደስታ ይኾናል!" ያለውን፡ የመምህራችን የኢየሱስ መሲሕን ቃል የመሰለ ኾነ። (ሉቃ. ፲፭፥ ፩-፲።)

ከዚህ በኋላማ፡ በዚያ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ሰውነት ውስጥ የሚሠራው፥ የሚገልጠው፥ መመሪያም የሚሰጠው፡ መንፈስ ቅዱስ ስለኾነ፡ ያን ሰውነት፡ የሚያሳስበው፡ አንዳችም ነገር፡ ከቶ የለም።

እንግዴህም፡ በቅዱሱ ኪዳን ወንድማችን ለኾንኸው፡ ለአንተ! ራስህን፡ ለዚህ እውነተኛ ማንነትህ በማብቃትህ፡ "እንኳን፡ ደስ አለህ!" እንልሃለን። ለ"እግዚአብሔር ይስጥልኝ!" ምርቃትህም፡ "አሜን!" ብለናል።

ከዚህ በተረፈ፡ ስላሠፈርሃቸው፡ ብዙዎች መልካካም ቃላት፡ እግዜር ይስጥልኝ!" እያልሁ፡ አያይዘህ ላቀረብሃቸው ተጨማሪ ጥያቄዎችህ፡ ከዚህ የሚከተሉትን መልሶች፡ ይኸው አበርክቼልሃለሁ፡-

እኛ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያ ተዋሕዶ አማኞች ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፡-

አ. ከኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ በወረስነው፡ የቃል ኪዳን ጸጋና በረከት ምክንያት፡ በእየራሳችን ባገኘነው፡ የእግዚአብሔር ልጅነትና ነጋሢነት፥ ክህነትም፡ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት፡ በቀጥታ፡ ከእናታችንና መድኃኒታችን፡ እግዝእተብሔር እም ድንግል ማርያም እና ከአባታችንና ሰላማችን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ጋር፡ ባለማቋረጥና በየአፍታው የምናካኺደው የንስሓ ግንኙነታችን፡ ቅጽበታዊ ነው። ይኸውም፡ በቤዛችንና በሰላማችን በኢየሱስ መሲሕ መስቀል፡ በስተቀኝ የተሰቀለው "ፈያታይ ዘየማን" የተባለው ወንበዴ፡ እንዳቀረበው፡ የአፍታ ንስሓ እና እንዳገኘውም የቅጽበት ስርየት ዓይነት ማለት ነው።

በ. አንቱታን የመሳሰሉትን የአክብሮት ቃላትን፡ ላላመኑ ሰዎች የምናውል ከመኾኑ በቀር፣ ደግሞም፡ በውስጣችን ያለው መንፈስ ቅዱሳችን የሚያሳስበንንና የሚነግረንን ተከትለን ከምንፈጽም በቀር፡ የትሕትና ቃላትን በመጠቀም ረገድ፡ እንደሌሎቹ ግብዞች ሃይማኖተኞች፡ ይህን ያህል አምነን የምንጨነቅበትና በተግባር ላይ የምናውለው፡ ልዩ ሥርዓት አለመኖሩን ልታውቀው ያስፈልጋል።

ገ. መጻሕፍቶቻችን፡ ለሽያጭም ኾነ ለምንባብ፡ እንደልብ ሊገኙ ያልተቻለው፡ የታተሙት ተሠራጭተውና ተሸጠው ስላለቁና ዳግመኛ ሳይታተሙ

በመቆየታቸው ስለኾነ፡ ይኸው ችግር ሊወገድ የሚችልበትን መፍትሔ በተግባር ላይ ለማዋል፡ ጥረታችንን በማጠናከር፡ በቅርቡ፡ ፍሬያማ ውጤት የሚገኝበትን ተልእኮ እንጀምር ዘንድ፡ መንፈስ ቅዱስ እንደሚያስችለን እናምናለን።

ደ. የግእዝን ትምህርት በሚመለከት፡ **በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት** ዘንድ ስላለው ዕቅድና ተግባር፡ ከዚህ በፊት፡ በተለያያ አቀራረብ ከተገለጸውና በሥራ ላይ ውሎ ከተበረከተው አገልግሎት ጋር፡ አኹን ደግሞ፡ ይኸው ዕቅድና ተግባር፡ ወደፊት በበለጠ መልክና በተጠናከረ ይዘት፥ በተስፋፋም መጠን ስለሚካኼድበት ዝግጅት፡ የመንፈስ ቅዱስን መመሪያ እንደምንጠብቅ ሳበሥርህ፡ ደስ ይለኛል።

በቅዱሱ ኪዳን ወንድምህና የአገልግሎት ተባባሪህ፡-
ኪዳናዊ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ [ንቡረ-እድ፡ ዘአኵስም-ጽዮን]።